ተገንዝበናል። የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የልጅነት ሁኔታ የለም ያለው አመልካቾች በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ መወለዳቸው አልተገለፀም፣ ሟች አመልካቾች የሟች ልጆች እንዳልሆኑ ገልፀው የተውት ኑዛዜ አመልካቾች እንዲፀድቅ መጠየቃቸው ልጆች አለመሆናቸውን ያመኑ መሆኑን ያሣያል በማለት ነው። ነገር ግን የልጅነት ሁኔታን ለማረጋገጥ ልጁ በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት መሆኑን ከማረጋገጥ ባለፈ ልጁ በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ለመሆኑ ማስረዳት አስፈላጊ አይደለም። በመሆኑም ሕጉ የማይጠይቀውን ተጨማሪ ሁኔታ አመልካቾች አላስረዱም በሚል የተሠጠው ውሣኔ አግባብነት የለውም።

ሌላው ሟች በተውት ኑዛዜ ላይ አመልካቾች ልጆች አለመሆናቸውን መግለፃቸው በራሱ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ አይደለም። የልጅነት ሁኔታ አለመኖሩን ለማስረዳት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 157/2/ መሠረት ልጅ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል ማስረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም ኑዛዜውን አመልካቾቹ እንዲፀድቅ መጠየቃቸው አመልካቾች የሟች ልጆች አይደሉም ወደሚለው መደምደሚያ አያደርስም።

በአጠቃላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካቾች የልጅነት ሁኔታ ያላቸው መሆኑን እያሳየ ሕጉ የማይጠይቀውን ተጨማሪ ሁኔታ አመልካቾች አላስረዱም በማለት የልጅነት ሁኔታ የለም በሚል የተሠጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው።

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4487 በሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26992 በሚያዝያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20534 በጥር 22 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

236 ሰበር መ/ቁ. 31430

ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ አዲስ አለም አከለ ቀርባለች።

**ተጠሪ** ፡- የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ ተወካይ ቀርቧል።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳውን የንብረት /ገንዘብ/ ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው። ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች እና ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ያደረጉ ሲሆን፣ ከዚህ ክፍፍል በኋላ ሊስማሙ ያልቻሉት ተጠሪ በብሩንዲ በሰላም ማስከበር ተግባር ላይ ተሰማርቶ ለነበረበት ጊዜ በድጐማ መልክ ተከፍሎታል በተባለው ገንዘብ ክፍፍል ላይ ነው። አመልካች ይህ ገንዘብ የተገኘው ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት /ፀንቶ በነበረበት ጊዜ/ እስከሆነ ድረስ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ስትከራከር፤ ተጠሪ ደግሞ ገንዘቡ ከደመወዝ የተለየና በድጐማ መልክ የተሰጠኝ በመሆኑ የግሌ ነው። ከባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሚደመር አይደለም በማለት ተከራክሮአል። ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የወረዳ ፍ/ቤት እና ይግባኙን የሰማው የከፍተኛ ፍ/ቤት ገንዘቡ የባልና ሚስቱ የጋራ

ሃብት ነው በማለት የወሰኑ ሲሆን፣ ለመጨረሻ ጊዜ ይግባኙን የሰማው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ግን የተጠሪን ክርክር በመቀጠል ገንዘቡ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት የሚባል አይደለም። ለክፍፍል አይቀርብም በማለት ወስኖአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

እኛም አመልካች ሰኔ 21 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በድጐማ መልክ ተገኘ የተባለው ገንዘብ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የማይሆንበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው። በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እንደምንመለከተው አከራካራው ገንዘብ በድጐማ መልክ ለተጠሪ የተከፈለው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ነው። አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ነጥብም ከዚህ ፍሬ ነገር የሚነሳ ሆኖ መወሰን ያለበት ደግሞ አግባብ ባለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ነው። በዚህ ረገድ አግባብ ያለው የቤተሰብ ሕግ የአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀጽ 73 እንደሆነ በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተመልክቶአል። ባልና ሚስት ተጋብተው አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ሠርተው፣ ጥረው፣ ግረው የሚያገኙዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ 73/1/ እና /2/ በግልጽ ስለመመልከቱም በፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ተገልጾአል። የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ሕጉ እንዲህ አይልም የሚል ምክንያት አልሰጠም። ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ነጥብ ገንዘቡ ባልና ሚስቱ በመረዳዳትና በመተጋገዝ በጋራ ያፈሩት ነው ሊባል አይችልም የሚል ነው።

በበኩላችን እንደምናየው ሕጉ ግልጽ ነው። ሕጉ ለጋራ ንብረት መሠረት ይሆን ዘንድ በዋነኛነት ያስቀመጠው በጋብቻው ጊዜ /ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ/ መገኘቱን ነው። ባልና ሚስቱ በጋብቻ ተሳስረው ባሉበት ጊዜ የሚገኘው ንብረት በሁለቱም የጋራ መተጋገዝ እንደተገኘ መቆጠር እንዳለበት ሕጉ ወስኗል። ባልና ሚስቱ በተለያየ ቦታ የመገኘታቸው ጉዳይ እግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም። ባል በአንድ ቦታ፤ ሚስት ደግሞ በሌላ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ቢኖሩ እንኳ ሕጉ የሚገምተው ሁለቱም ለትዳራቸው እኩል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብሎ ነው። በመሆኑም ንብረቱ በሕጉ ተቀባይነት ባለው አግባብ የአንዱ ተጋቢ ወገን የግል ሃብት መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ በጋብቻው ወቅት የተገኘው ንብረት ሁሉ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው የሚሆነው። በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም ተጠሪ በድጐማ ተሰጠኝ የሚለው ገንዘብ የጋራ ሀብት የማይሆንበት የሕግ ምክንያት የለም። ከዚህ የተነሳም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 1046/98 ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል።
2. ለተጠሪ በድጐማ መልክ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ በባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሚካተት በመሆኑ አመልካች እና ተጠሪ እኩል ይካፈሉት ብለን ወስነናል።
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይበለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ዙ/ዘ